የመላው ዐማራ ሕዝብ ፓርቲ
**All Amhara People’s Party**

የአማራ ዴሞክራሲያዊ ሃይል ንቅናቄ
**Amhara Democratic Movement Force**

# በወቅታዊ ጉዳዮች ላይ ከመዐሕፓ እና አዴኃን የተሰጠ የጋራ መግለጫ

ሐሙስ ሐምሌ 4 ቀን 2011 ዓ.ም.

ራስ አምባ ሆቴል፣ አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ

ቅዳሜ ሰኔ 15 ቀን 2011 ዓ.ም በባህር ዳር ከተማ የተከሰተው ክስተት በእጅጉ አሳዝኖናል፡፡ ከመሪዎች ግድያ ባሻገር በችግሩ መንስዔ እና ውጤት ላይ ከግራም ከቀኝም የሚሰጡ አወዛጋቢ ትንታኔዎች፣ አሉባልታዎች እና ፍረጃዎች እጅጉን አድምተውናል፡፡ ቢሆንም በወንድሞቻችን ሞት ለተጎዳው ቤተሰባቸው፣ ወዳጅ ዘመዶቻቸው እንዲሁም የዐማራ ሕዝብ መጽናናት እና ብርታት በድጋሚ እንመኛለን፡፡

የችግሩ ምንጭ በአዴፓ አመራር መካከል በተፈጠሩ የመፍትሔ አማራጮችና አቅጣጫዎች ላይ የአቋም ክፍተት እና ግጭት ይሁን ወይም ሌላ ውጫዊ ኃይል ምክንያት  ተጠያቂነቱን ላለመቀበል ወይም ከዚህ ተሞክሮ ላለመማር የክስተቱን አድማስ እና ውጤት በማስፋት እየተሔደበት ያለው ርቀት ከተጠያቂነት አያድንም፡፡ ችግሩ ከተከሰተበት አውድ ከባህር ዳር በመነሳት አድማሱን በመላው አማራ ብሎም ኢትዮጵያ በመለጠጥ በችግሩ ግንኙነት ሊኖራቸው ይችላል ተብለው የማይታሰቡትን ጋዜጠኞች፣ አክቲቪስቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላትን፣ የሙብት ተሟጋቾችን፣ ባለሐብቶች የተወሳሰበ ሰበብ በማበጀት መንግስት የሚያደረገው  እርምጃ አጥብቀን እንቃወማለን፡፡ እስከአሁን ከፍተኛ ቁጥር ያላቸው ዜጎች ታስረዋል፡፡ ይህ ቁጥር የአማራ ክልል አመራሮች፣ ጋዜጠኞች፣ አክቲቪስቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮችና አባላት፣ የወጣት ማኅበራት አመራሮች፣ የሙብት ተሟጋቾች እና ባለሐብቶችን ያካተተ ሲሆን አካባቢያዊ አድማሱ መላውን ዐማራ፣ ወሎ፣ ጎጃም፣ ሻሸመኔ፣ አሰላ፣ አሰበ ተፈሪ፣ ጨለንቆ፣ ቁልቢ፣ ደደር፣ ሱሉልታ፣ ቡራዩ፣ ለገጣፎ፣ ፉሪ፣ ዓለም ገና፣ ናዝሬት፣ ባሌ፣ መቱ፣ ፍቼ፣ አሶሳ እና ሌሎች አካባቢዎች ይሸፍናል፡፡

ከዚህ ባለፈ በሽብር ወንጀልም ሆነ ከተፈጠረው ችግር ጋር የተወሳሰበ እና እርስ-በርሱ የሚጣረስ ሰበብ እየተፈጠረ፣ የችግሩን አድማስ የማስፋት እና የማሸማቀቅ ሒደት ቀጥሏል፡፡ ዜጎች ከፍርድ ቤት ውሳኔ በፊት አስቀድሞ ወንጀለኛ ተብለው የሚፈረጁበትን መንገድና ብያኔ ተስተውሏል፤ ህግ የሚፈቅድላቸውንም በ48 ሰዓታት ወደፍርድ ቤት የመቅረብ መብት በከፋ ሁኔታ ተጥሷል፡፡

የፌደራል መንግስት ክልሉ ያለውን ራስን የማስተዳደር እና የመምራት ስልጣን በመጣስ ጣልቃ በመግባት የመከላከያ እና የፌደራል ፖሊስ በአካባቢው አሰማርቷል፡፡ ይህም የሕዝቡን የተረጋጋ ስሜት እና ፍላጎት በከፍተኛ ሁኔታ ረብሾታል፡፡ የተፈጠረውን ችግር ከአድማሱ በላይ በመለጠጥ እና በማጋነን አካባቢው እንዳይረጋጋ እና ሕዝቡ ላይ ስነልቡናዊ ጫና ፈጥሯል፡፡ በሕዝቡ መካከል ነገ ምን ይፈጠር ይሆን የሚለው ጭንቀት ከፍተኛ ነው፡፡ የመከላከያና የፌደራል ፖሊስ በአካባቢው መቆየት በክልሉ አመራር ላይ የነበረውን አመኔታ ጨርሶ እንዳያሟጥጠው ስጋት አለን፡፡

ይህንን አጋጣሚ በመጠቀም ወደከፋ የእርስ-በርስ ትርምስ ለመምራት፣ የዐማራውን ሞራል ለማሸማቀቅ እና ሰብዕናውን ለማጠልሸት እንደሕዝብ አንገት ለማስደፋት ለሚጥሩ አካላት ሁሉ አማራውን አጋልጦታል፡፡ “የዐማራን የበላይነት ለማምጣት የሚያስቡ ኃይሎች የፈጠሩት ችግር ነው” ብለው የሴራ መርዛቸውን ከሚዘሩት አሜሪካዊው ኸርማን ኮህን እስከ ነፃነት እና እኩልነት እንቆማለን ባይ ወንድሞቻችን ድረስ የተለጠጠ እንድምታና ምስል  ማላበስ ከፍተኛ ግምት እንድንወስድ አድርጎናል፡፡ እነዚህ አካላት አማራው ለነፃነት፣ ለእኩልነት እና ለፍትሕ የሚያደርገውን ትግል በማዛባት የፖለቲካ ትርፍ የሚቆምሩበት ዘመን ያከተመ መሆኑን አልተረዱትም፡፡ የአማራው ችግር እና ሕልውና በሰከነ መንገድ እልባት እንዲያገኝ የሚቀርቡ ጥያቄዎች ምላሽ እንዳያገኙ የሚታትሩ ናቸው፡፡ በአንድ ሀገር ውስጥ አንድ ሕዝብ የሚያንገበግበው ችግር የዚያ ሕዝብ ብቻ ሆኖ አይቀርም፡፡ እነዚህ አካላት አማራው ችግሩን እንዳይጠይቅ “ትምክህተኛ” ብለው በደምሳሳው ያጠቁሩታል፡፡ ትክክል አይደም፡፡ ሕዝብ በደምሳሳው አይፈረጅም፡፡ የሁላችንም ነፃነት፣ እኩልነት  እና ክብር አብሮ የሚያድግበትን መንገድ መተለም እና ማሳየት እንጂ በጎራ እየተመዳደቡ በየአጋጣሚው መጠማጠም እና መጠላለፍ ማብቃት አለበት እንላለን፡፡

በባህር ዳር በተፈጠረው ችግር ከማዘን እና ከመተከዝ እንዲሁም የክልሉ መንግስት ብቻውን እንዲወጣ ከመተው በዘለለ ጊዜያዊም ሆነ ዘላቂ መፍትሔ ማምጣት የምንችል፣ ኃላፊነትም የሚጠበቅብን መሆኑን በማመን ለሚከተሉት ባለድርሻዎች የጋራ ጥሪ እናቀርባለን፡፡

**<u>ለአማራ ክልል መንግስት፤</u>**

የተፈጠረው ችግር የሚያደርሰውን ጫና በመቋቋምና በመረጋጋት የተፈጠረውን የአመራር ክፍተት ከማንኛውም ተፅዕኖ ነፃ በሆነ መንገድ እንዲያሟላ እና ክልሉን በማረጋጋት የመከላከያ እና ፌዴራል ፖሊስ ከክልሉ እንዲወጣ እንጠይቃለን፡፡ የክልሉንም ራሱን የማስተዳደር ስልጣን እና አቅም እንዲያረጋግጥ አጥብቀን እንጠይቃለን፡፡ የተፈጠረውንም ችግር መንስዔ በተጠያቂነት እና እውነት ላይ ብቻ ተመርኩዞ ከተለያዩ ባለድርሻዎች በተውጣጣ አጣሪ ኮሚቴ እና ሕብረተሰቡን ባሳተፈ መንገድ እንዲጣራ እንጠይቃለን፡፡ ይህ ችግር ያደረሰብን ጉዳት እንደተጠበቀ ሆኖ ሌላ ቀውስ እንዳያስከትል የመፍትሔ ባለድርሻዎች ማለትም በአማራነት የተደራጁ የፖለቲካ ኃይሎች፣ ምሁራን፣ የወጣት ማኅበራት፣ የሐይማኖት ተቋማትን ያቀፈ ሕዝባዊ የምክክር መድረክ በአስቸኳይ እንድናዘጋጅ እና ሕዝቡን እንድናረጋጋ እንጠይቃለን፡፡ ተጨባጭ መረጃዎችን ለሕዝብ በማድረስ ከአደናጋሪ እና ስሁት መረጃዎች፣ መግለጫዎች እና ድርጊቶች ሕዝባችንን እንድንጠብቅ እንጠይቃለን፡፡ በወንጀል የተጠረጠሩትን በመለየት እና በ48 ሰዓታት ውስጥ ወደፍርድ ቤት የሚቀርቡበትን ህጋዊ ኃላፊነት እንዲወጣ፤ ከአሁን በፊትም ተጠርጥረው የተያዙትን በ48 ሰዓታት ሳያቀርብ የቀረበት ምክንያት ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርግ፡፡ አጋጣሚውን በመጠቀም ለፖለቲካ ትርፍም ይሁን ለማረጋጋት ሲባል የታሰሩ አክቲቪስቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የመብት ተሟጋቾች፣ ባለሐብቶች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት በአስቸኳይ እንዲፈቱ፡፡ የተፈጠረውን ችግር ለማረጋጋት እና ዘላቂ መፍትሔዎችን ለመሻት ከባለድርሻዎች ጋር የምክክር መድረክ ለማዘጋጀት በድርሻችን እየተንቀሳቀስን ሲሆን በዚህ ረገድ የክልሉ መንግስት ለሚያደርጋቸው ማናቸውንም እንቅስቃሴዎች ለመደገፍ ዝግጁነታችንን ማሳወቅ እንወዳለን፡፡

**<u>ለፌደራል መንግስት፤</u>**

መንግስት ከፖለቲካ ፍጆታ በዘለለ በወንጀሉ የተጠረጠሩትን በመለየት እና በ48 ሰዓታት ውስጥ ወደፍርድ ቤት የማቅረብ ህጋዊ ኃላፊነቱን እንዲወጣ ከአሁን በፊትም ተጠርጥረው የተያዙትን ለምን በ48 ሰዓታት ሳያቀርብ የቀረበት ምክንያት ለሕዝብ ይፋ እንዲያደርግ፡፡ አጋጣሚውን በመጠቀም ለፖለቲካ ትርፍ ሲባል የታሰሩ አክቲቪስቶች፣ ጋዜጠኞች፣ የመብት ተሟጋቾች፣ ባለሐብቶች እና የፖለቲካ ፓርቲ አመራሮች እና አባላት በአስቸኳይ እንዲፈቱ፡፡ ክልሉም የተረጋጋ ስለሆነ የመከላከያ እና የፌደራል ፖሊስ አካላትን እንዲያስወጣ፡፡

**<u>ለዐማራ ሕዝብ፤</u>**

የዐማራ ሕዝብ በችግር ጊዜ ተለባብሶ፣ በአደጋ ጊዜ ተደጋግፎ፣ በወረራ ጊዜ ተጠራርቶ አገር የሚጠብቅ ሕዝብ ነው፡፡ በፍትሕም ሆነ በፈሪሃ-እግዚአብሔር በስርዓት የሚኖር ነው፡፡ ከማንኛውም ሕዝብ እና በየትኛውም ዓለም ተዋኀዶ እና ተመሳስሎ በእኩልነት የሚተዳደር ሕዝብ ነው፡፡

በዚህ ወቅት ባሳየው መረጋጋት ችግሩን እና የሚያጋጥመውን መከራ መሻገር እንደሚችል አረጋግጧል፡፡ አሁንም ቢሆን በመረጋጋት እና አካባቢውን በንቃት በመቆጣጠር፣ በመመካከር ወደከፋ ችግር እንዳያድግ ማድረግ የሚቻልበትን መንገድ እንዲደግፍ፣ አላስፈላጊ ጣልቃገብነትን እና ከፋፋይ አሉባልታዎችና ፕሮፖጋንዳዎች ራሱን እንዲጠብቅ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**<u>ለሲቪክ አደረጃጀቶች (ወጣቶች፣ መምህራን፣ ተማሪዎች፣ አርቲስቶች፣...)</u>**

ይህ ወቅታዊ ችግር መፈጠር አማራው የተረጋጋ፣ የተናበበ እና በአንድነት የጠነከረ አደረጃጀት እና ትግል እንዳይኖረው ብሎም ለደቂቃ እንኳን የሰከነ አስተሳሰብ፣ ደስታ እና ኑሮ እንዳይኖረው አስቷጽኦ አለው፡፡ "የጨው ጋራ ሲናድ ሞኝ ይልሳል፤ ብልህ ያለቅሳል" እንዲሉ፡፡ አማራው አንገቱን እንዲደፋ፣ ችግሩን ወደሌላ ቀውስ ለመንተት የሚፈልጉ ኃይሎች ከውስጥም ከውጪም እንዳሉ ስንመለከት ከመቼውም በላይ በአንድነት መቆም ግድ ይለናል፡፡ በዚህ ወቅት ጠላት በሚወረውርልን የመናቆርና የመቆራመድ አጀንዳ ሳንገደብ በከፍተኛ ኃላፊነት እና ጥንቃቄ ማኅበረሰባችን ከአሉባልታ፣ ችኩልነት እና ስሜታዊነት እንዲርቅ እና በአንድነት መቆም እንዳለብን ማሳሰብ እንወዳለን፡፡ በተፈጠረው ችግር ላይ በየአካባቢው ከሚገኘው የአስተዳደር መዋቅር እና የሕብረተሰብ ክፍሎች ጋር ተናብቦ መሥራት ይጠበቅብናል፡፡ መፍትሔ ጠባቂዎች ሳንሆን አፍላቂዎች ሆነን በአካባቢያችን ላይ ስለሚደረጉ ማናቸውም ድርጊቶች እና እንቅስቃሴዎች በኃላፊነት እና በራስ መተማመን መንቀሳቀስ ያስፈልጋል፡፡ የተፈጠረው ችግር አንድ ጊዜ ተከስቷል፤ ይህ ችግር ሌላ ቀውስ እንዳያስከትል የተለያዩ ሕዝባዊ የምክክር መድረኮች በማዘጋጀት እና በመመካከር ይህንን ጊዜ በእርጋታ፣ በማስተዋል እና በአንድነት እንድንሻገር ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡

**<u>ለአማራ የፖለቲካ ፓርቲዎች፤</u>**

አማራው የተናበበ እና የጠነከረ አደረጃጀት እንዳይኖረው ካደረጉት ችግሮች መካከል በመግባባት እና በመደጋገፍ አለመመራት ነው፡፡ የተፈጠረው ችግር የአማራውን ሕዝብ የፖለቲካ እና ማህበራዊ ተሳትፎ መነቃቃት መልሶ የሚያዳፍን ነው፡፡ በተለይ ከችግሩ ማግስት እየተወሰዱ የሚገኙ እርምጃዎች አሳሳቢ ናቸው፡፡ ስለዚህ በአማራነት የተደራጁ የፖለቲካ ፓርቲዎች በአሁኑ ወቅት የተፈጠረውን ችግር በጋራ በመመካከር የጋራ መፍትሔ እንድንወስድ ጥሪያችንን እናቀርባለን፡፡ ቀደም ሲል ጥሪ ላቀረባችሁ ጥሪያችሁን በደስታ ተቀብለን ወደተግባር እንገባ ዘንድ ይህንን የሚመራ የጋራ ኮሚቴ አባላት ከዛሬ ጀምሮ እንቅስቃሴ የጀመሩ መሆኑን ማሳወቅ እንወዳለን፡፡

ዐማራ በልጆቹ ትግል ታሪኩን ያድሳል!
ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል-ኪዳን ነው!